# IMPACT EAST COLFAX

the fax

URBAN LAND CONSERVANCY

## የማኅበረሰብዎን አባላት ሕይወት በሚሻሽል የከተማ ልማት ሀሳብ ይደሰታሉ?

## አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን የኢስት ኮልፋክስ መንደሮችን በደንብ ያውቃሉ?

## በከታማ እቅድ፣ ሪል እስቴት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ ቤቶች ልማት ወይም ግንባታ የሥራ ልምድ አለዎ?

## በኢስት ኮልፋክስ ላይ በሚካሄድ ልማት ተጽዕኖ ወይም ጉዳት የደረሰባቸውን ማኅበረሰቦች ፍላጎቶች መወከል ይችላሉ?

ከእነዚህ ጥያቄዎች ለአንዱ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑት አዎ ብለው ከመለሱ ለኢስት ኮልፋክስን እንለውጥ (Impact East Colfax) የስቲሪንግ ኮሚቴ አባል ሆነው ለመስራት ፍላጎት ሊኖርዎ ይችላል!

## የኢስት ኮልፋክስ ጎዳና ኮሪዶር

በኮሎራዶ ቡለቫርድ እና በ I-225 መካከል ያለው 6-ማይል ቦታ ንቃት እና ብዝሃነት ያላቸው ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች፣ ባህሎች፣ ንግዶች እና የማኅበረሰብ ድርጅቶች መገኛ ነው። በታቀደው የፈጣን አውቶብስ መስመር ፕሮጀክት እና እንደመጥፎ አጋጣሚ ሆኖ አሁን በአካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎች እና ንግዶች የመፈናቀል ስጋታቸውን የሚጨምረው በቅርቡ በታቀደው የእድል ዞን ልየታ አማካኝነት ኢስት ኮልፋክስ ለተሳለጠ መሠረተ ልማት እና ግብዓቶች ታጭታለች።

ለውጥ ለኢስት ኮልፋክስ (IMPACT EAST COLFAX) አሁን በኮሪዶሩ ውስጥ የሚገኙትን ማኅበረሰቦች ፍትሃዊ እና ተመጣጣኝ የንግድ እና የመኖሪያ ቤቶችን በኢስት ኮልፋክስ ኮሪዶር ላይ በማልማት ለመታደግ የተፈጠረ የከተማ መሬት ቁጠባ (ULC) እና የፋክስ አጋርነት (The Fax) ትብብር ነው። ርዕዩን ለማሳደግ፣ አቅጣጫ ለመስጠት እና የፕሮጀክቶቹን ግንባታ ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ ትብብሩ **ሁለት ማኅበረሰብ-ተኮር የስቲሪንግ ኮሚቴዎችን** (አንድ ለዴንቨር እና አንድ ለአሮራ) በማቋቋም ላይ ይገኛል።

**ዛሬውኑ ያመልክቱ!** የስቲሪንግ ኮሚቴ አባላት የመስብሰቢያ አበል የሚከፈላቸው ሲሆን ለሁለት ዓመት የሥራ ዘመን ማገልገል ይጠበቅባቸዋል። ለማመልከት የመጨረሻው ቀን ኢፕሪል 30፣ 2021 ነው።ስለ ለውጥ ለኢስት ኮልፋክስ (Impact East Colfax) ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እና ለአንደኛው የስቲሪንግ ኮሚቴ አባል ለመሆን ለማመልከት ይህን ድር ጣቢያ ይጎብኙ፦ Visit www.urbanlandc.org/community-updates።

